# ምቹ የሥራ ቦታን መፍጠር በተመለከተ የልምድ ልውውጥ መድረክ ተካሄደ

በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የጫማ ኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት አስተባባሪነት በጥር 16, 2010 ዓ.ም ከህንድ በመጣ ኤክስፐርት ምቹ የስራ ቦታን መፍጠር በተመለከተ ከ25 ባለሙያዎች ጋር የልምድ ልውውጥ ተደረገ፡፡ ሚስተር ፓራሳና ኤስ ራኦ የስራ ቦታ ተስማሚነት ምን እንደሆነ፣ ለስራ ቦታ ተስማሚነት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች እና የስራ ቦታ ተስማሚነት ኤስ ኤ 8000 ደረጃ አስገዳጅ ዝርዝሮች በተመለከተ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ በሌላ ርዕሰ ጉዳይ ባለሙያው የአካባቢ ደህንነትን በተመለከተ ገለጻ የሰጡ ሲሆን በተለይም ይህ ጉዳይ ከኢንዱስትሪ ጋር ተያያዥነት ያለው እንደመሆኑና አይ ኤስ ኦ 14001 ብክለትን ስለመከላከል የሚያተኩርና ብክለትን ከመቆጣጠር ህጋዊ መዕቀፎች ጋር የሚስማማ መሆኑን ክትትል በማድረግ የተቋምን የአካባቢ ደህንነት ስራ በቀጣይነት እንዲሻሻል እንደሚያግዝ አመላክቷል፡፡

ባለሙያው የአካባቢ ደህንነት ስርዓት የአካባቢ ብክለት ትኩረታቸው ለሆኑ ኢንዱስትሪዎች ብክለትን ስልታዊ በሆነ ዘዴ መከላከል እንዲችሉ በጣም አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በገለጻው እንደዚሁ የሥራ ቦታ ጤናና ደህንነት ሁኔታዎች እና የሰራተኞችን ወይም ጊዜያዊ ሰራተኞችን እና ጎብኚዎች ጨምሮ ሌሎችን ጤናቸውንና ደህንነታቸውን ሊጎዱ የሚችሉ ምክንያቶች አስመልክቶ ተብራርቷል፡፡

በመድረኩ የስራ ቦታ ምቹነትን አስመልክቶ የህንድና የባንግላዲሽ ተሞክሮ በባለሙያው ቀርቧል፡፡ ተሳታፊዎች ከገለጻ በኋላ አንዳንድ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ያነሱ ሲሆን ከነዚህ መካከል የኢትዮጵያና የሌሎች አገሮች ኤክስፖርት አፈጻጸም፣ ለተቋሙ ሰራተኞች የቀረቡ የስራ ደህንነት መጠበቂያ ማቴሪያሎች በተመለከተ፣ለአካል ጉዳተኞች የሚያመች የስራ ቦታ ከመፍጠር አንጻር ካምፓኒዎችን እንዴት ማስገደድ እንደሚቻል እና ይህን መሰል የልምድ ልውውጥ መድረክ ወደፊትም መቀጠል እንዳለበት የሚሉት ይገኙባቸዋል፡፡

በመጨረሻ ሚስተር ፓራሳና ለተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ እና ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን በተለይም የስራ ቦታ ተስማሚነትን በጫማ ፋብሪካዎች በተሻለ የአቅም ማሳደጊያ ፕሮግራም ማጠናከር አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡